የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አራተኛ ዓመት ቁጥር ፶፪
አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፪ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

24th Year No.52
ADDIS ABABA, 3rd August 2018

<u>ማውጫ</u>

**አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፺፭/፪ሺ፲ ዓም**

የድሬዳዋ አስተዳደር ቻርተር (ማሻሻያ) አዋጅ.....................................................ገፅ ፲ሺ፫፻፺፰

**<u>CONTENT</u>**

**PROCLAMATION No. 1095/2018**

Dire Dawa Administration Charter (Amendment) Proclamation..............................................................page

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፺፭/፪ሺ፲

## <u>የድሬዳዋ አስተዳደር ቻርተር አዋጅን( እንደተሻሻለ) ለማሻሻል የወጣ አዋጅ</u>

የተሻሻለው የኢትዮጵያ ምርጫ ህግ አዋጅ ቁጥር ፭፻፴፪/፲፱፻፺፱ በአንቀጽ ፳፰ ንኡስ አንቀጽ (፩) ላይ ጠቅላላ ምርጫ በየአምስት ዓመቱ የሚፈጸም መሆኑን የሚደነግግ በመሆኑ፤

የድሬዳዋ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ( እንደተሻሻለ) ቁጥር ፬፻፲፮/፲፱፻፺፮ አንቀጽ ፯ ላይ ምርጫን አስመልክቶ በመስተዳደሩ የሚከናወኑ ምርጫዎች በሀገሪቱ የምርጫ ህግ መሰረት እንደሚከናወኑ የሚደነግግ በመሆኑ፤

የድሬዳዋ አስተዳደር ምክር ቤት የስራ ዘመኑ ሰኔ ፴ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም የሚጠናቀቅ ሲሆን በድጋሚ ካልተመረጠ ወይም የሕግ ማሻሻያ ካልተደረገ በስተቀር ቀጣይ ሥራ ለመስራት ሥልጣን ስለማይኖረው ምርጫ እስከሚከናወን ድረስ ሥራውን እንዲቀጥል የሕግ ማሻሻያ ማድረግ በማስፈለጉ፤

ምርጫ ተከናውኖ ምክር ቤት እስከሚደራጅ ድረስ አሁን ያለው ምክር ቤትና ስራ አስፈፃሚ ስራውን

## PROCLAMATION No. 1095/2018

## <u>A PROCLAMATION TO AMEND THE DIREDAWA ADMINISTRATION REVISED CHARTER /AS AMENDED/ PROCLAMATION</u>

**WHEREAS,** it is provided for under sub article 1 of Article 28 of the Electoral Law of Ethiopia Amendment Proclamation No. 532/2007 (as amended), general election shall be conducted every five years;

**WHEREAS**, it is stipulated under Article 7 of the Dire Dawa Administration Charter Proclamation No. 416/1996 (as amended), election for the Council at all levels of the City Government shall be conducted in accordance with the electoral law of the country;

WHEREAS, it is found important to amend the law, unless the council of Dire Dawa city administration council is reelected or an amendment of the law is made, the Council shall not have the power to discharge its duty as the term of Office of the Council expires on July 7 /2018;

**WHEREAS,** it is found important to retain the existing Council and the executive organs to discharge its duties until election is conducted;

ይዞ እንዲቀጥል ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በምክትል ከንቲባነት መስተዳደሩን ለመምራት ብቃት ያለውን ሰው ከምክር ቤቱ አባላት ወይም ከምክር ቤት አባላት ውጪ ለመሾም ዕድል የሚሰጥ ድንጋጌ ማካተት በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**፩.** **<u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "የድሬዳዋ አስተዳደር ቻርተር (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፺፭/፪ሺ፲" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪.** **<u>ማሻሻያ</u>**

የድሬዳዋ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፬፻፲፮/፲፱፻፺፮ (እንደተሻሻለ) እንደሚከተለው ተሻሽሏል:-

፩/ የአዋጁ አንቀጽ ፲፫ ንዑስ አንቀጽ (፩) እንደሚከተለው ተሻሽሏል:-

"፩/ የምርጫ ቦርድ በሚወስነው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት አዲስ ምርጫ እስከሚካሄድ ድረስ የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን ተራዝሟል፡፡"

፪/ የአዋጁ አንቀጽ ፳፩ ንዑስ አንቀጽ (፪) እንደሚከተለው ተሻሽሏል:-

"፪/ ምክትል ከንቲባው ከምክር ቤት አባላት ውስጥ ወይም ከምክር ቤት አባላት ውጭ ሊሾም ይችላል፡፡"

፫/ በሥራ ላይ የሚገኙ በሕግ የተቋቋሙ የድሬዳዋ አስተዳደር የመንግስት አካላት ምርጫ እስከሚካሄድ ድረስ ተግባርና ኃላፊነታቸውን መወጣት ይቀጥላሉ፡፡

**፫.** **<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**WHEREAS,** it is found important to incorporate a provision which allows appointment of competent Deputy Mayor either from the members of the Council or none members of the Council;

**NOW THEREFORE**, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

**1.** **<u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the "Dire Dawa Administration Charter (Amendment) Proclamation No.1095/2018".

**2.** **<u>Amendment</u>**

The Dire Dawa Administration Charter Proclamation No. 416/1996 (as amended) is hereby amended as follows:

1/ Sub-article (1) of Article 13 of the Proclamation is amended as follows:

"1/.The term of Office of the Council shall be extended until new election is conducted in accordance with the time table to be set by the National Electoral Board."

2/ Sub-article (2) of Article 21 of the Proclamation is amended as follows:

"2/.The Deputy Mayor shall be appointed either from the Members of the Council or from nonmembers of the Council."

3/The existing Dire Dawa Administration Government organs established by law shall continue to discharge their duties and responsibilities until election shall be held.

**3.** **<u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force on the date of approval by the House of Peoples' Representatives.

**Done at Addis Ababa, 3rd day of August 2018**

**MULATU TESHOME (Dr.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፪ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም**

**ሙላቱ ተሾመ (ዶ/ር)**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ**

**ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**